የኢየሱስ ምሳሌያዊ አስተምህሮዎች

የመንግሥተ ሰማይ ምሥጢራት መፍቻ

ዶክተር ጄ. ድዋይት ፐንተኮስት
Dr. J. Dwight Pentecost

ተርጓሚ አቢይ ደምሴ

Published by
LAPSLEY/BROOKS FOUNDATION
Addis Ababa --- Dallas, Texas
Ethiopia U.S.A.
1989 - 1997

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
1989 (1997 እ.አ.አ.)

ይህ መጽሐፍ የተተረጎመው፡-
"The Parables of Jesus"
by Dr. J. Dwight Pentecost
Copyright 1982
Zondervan Corporation
Grand Rapids, Michigan, U.S.A.
ከሚለው መጽሐፍ ሲሆን
የታተመውም በደራሲው ፈቃድ ነው።

የላፕስሊ/ብሩክስ ፋውንዴሽን
ሰልክ 201464፣ ፖስታ 41221
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
Publisher
Lapsley/Brooks Foundation
Dallas, Texas, U.S.A.

አንደኛው እትም የቀረበው "የኢየሱስ ምሳሌዎች"
በሚል ርእስ ነው
ሁለተኛ እትም 1992 ዓ.ም. (2000 እ.አ.አ.)

የመጽሐፍ ማውጫ

መቅድም 9

መግቢያ 10

1. ባለ መድኃኒቱ 21
   ሉቃስ 4፡23

2. እራፊው ልብስና ያረጀው አቁማዳ 24
   ማቴዎስ 9፡16-17፤ ማርቆስ 2፡21-22፤ ሉቃስ 5፡36-39

3. ዕውራን መሪዎች 27
   ማቴዎስ 7፡3-5፤ ሉቃስ 6፡39-42

4. ብልሁና ሰነፉ ቤት ሠሪዎች 29
   ማቴዎስ 7፡24-29፤ ሉቃስ 6፡43-49

5. ገበያ ውስጥ የሚቀመጡ ልጆች 31
   ማቴዎስ 11፡16-19፤ ሉቃስ 7፡29-35

6. ሁለቱ ተበዳሪዎች 33
   ሉቃስ 7፡41-50

7. የክርስቶስን እሱነት የሚያረጋግጡ ምሳሌዎች 36
   ማቴዎስ 12፡22-30፤ ማርቆስ 3፡22-27

8. ባዶው ቤት 39
   ማቴዎስ 12፡43-45

9. የመንግሥቱን አዲስ ቅርጽ የሚመለከቱ ምሳሌዎች 42

10. ዘሪው፡ የሚዘራው ፍሬና መሬቱ 46
    ማቴዎስ 13፡3-23፤ ማርቆስ 4፡3-25፤ ሉቃስ 8፡15-18

11. ታዳጊው ቡቃያ 49
    ማርቆስ 4፡26-29

12. እንክርዳዶቹ 50
    ማቴዎስ 13፡24-30

13. የሰናፍጭ ዘር 52
    ማቴዎስ 13፡31-32

14. ከዱቄት የተደባለቀ እርሾ 54
    ማቴዎስ 13፡33

15. እርሻ ውስጥ የተሰወረው መዝገብና መልካሙ እንቁ 56
ማቴዎስ 13፡44-45
16. መረቡ 59
ማቴዎስ 13፡47-50
17. የቤቱ ጌታ 60
ማቴዎስ 13፡52
18. ክፉው አገልጋይ 62
ማቴዎስ 18፡21-35
19. መልካሙ እረኛ 65
ዮሐንስ 10፡1-18
20. መልካሙ ሳምራዊ 68
ሉቃስ 10፡30-37
21. ጎትጓቹ ወዳጅ 73
ሉቃስ 11፡1-10
22. ሞኙ ባለጸጋ 76
ሉቃስ 12፡16-21
23. ትጉሆቹ አገልጋዮች 80
ሉቃስ 12፡35-40
24. ፍሬ አልባዋ የበለስ ዛፍ 83
ሉቃስ 13፡6-9
25. የሠርጉ ግብዣ ስፍራ መቀመጫዎች 86
ሉቃስ 14፡7-11
26. ታላቁ ድግስ 89
ሉቃስ 14፡16-24
27. ግንበኛው ሰውዬና ጦረኛው ንጉሥ 93
ሉቃስ 14፡25-33
28. በጉን የሚፈልገው እረኛ፥ ድሪሚን የምትፈልገው ሴት፥ እና ልጁን የሚጠባበቀው አባት 96
ሉቃስ 15፡1-32
29. ልባሙ መጋቢ 105
ሉቃስ 16፡1-13
30. ባለጠጋውና አንድ ድሀ ሰው 108
ሉቃስ 16፡19-31

31. የማይጠቅም ባሪያ 112
ሉቃስ 17፡7-10
32. ያልታከተችው መበለት 114
ሉቃስ 18፡1-8
33. ፈሪሳዊውና ቀራጩ 116
ሉቃስ 18፡9-14
34. የወይኑ አትክልት ስፍራ ሠራተኞች 122
ማቴዎስ 20፡1-16
35. አሥሩ ምናኖች 126
ሉቃስ 19፡11-27
36. ሁለቱ ልጆች 130
ማቴዎስ 21፡28-32
37. የወይኑ አትክልት ስፍራ ባለቤት 132
ማቴዎስ 21፡33-44
38. የሠርጉ ድግስ 136
ማቴዎስ 22፡1-14
39. የበለሲቱ ዛፍ 140
ማቴዎስ 24፡32-34
40. በረኛው 143
ማርቆስ 13፡33-37
41. ጥንቁቁ ባለቤት እና ልባሙ አገልጋይ 145
ማቴዎስ 24፥ 42-51
42. አሥሩ ልጃገረዶች 148
ማቴዎስ 25፡1-13
43. መክሊቶቹ 151
ማቴዎስ 25፡14-30
44. በጎቹና ፍየሎቹ 153
ማቴዎስ 25፡31-46
45. በምሳሌዎቹ የተጠቀሰው መንግሥት ትምህርተ-ሃይማኖት ትርጓሜ 157
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ማውጫ 176

ምስጋና

ይህ የትርጉም ሥራ ዳር እንዲደርስ ሞያዊ እርዳታ በመስጠት ረገድ የተሳተፉትን ኢትዮጵያውያን በሙሉ፥ በተለይም ጽሑፉን በማረም የረዱንን፥ አቶ ተክሌ ገብረ መድህን፥ ጀን ከምበርስ፥ ትፍስህት ለማ፥ እንግዳሽ ማርቆስ እና ኤዲተር ገበየሁ አየለን ከልብ እናመሰግናለን።

ማሳሰቢያ

- የመጽሐፉ ተርጓሚ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ አንዳንድ ክፍሎችን ግልጥ ለማድረግ ሲል በደራሲው ፈቃድ አንዳንድ ማብራሪያዎችን ጨምሯል።

- በዚህ መጽሐፍ፥ ከመዝሙረ ዳዊት ከምዕራፍ 10-146 ውስጥ የተጠቀሱ ጥቅሶች ሁሉ ከድሮው (1954 ዓ.ም.) መጽሐፍ ቅዱስ በቅንፍ የተጠቀሱትን ምዕራፎች ያመለክታሉ።

- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ ከሚገኙበት የገጽ ቁጥር ጋር በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ በ"ጥቅስ ማውጫ" ላይ ቀርበዋል።

- "ሰማይ" የሚለውን ፅንሰ-አሳብ ለመግለጥ የሚያገለግለው የግሪክኛ ቃል 'ኡራናስ' ['ouranos'] ነው። ይህ ቃል አንዳንድ ጊዜ በብዙ ቁጥርም ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን፥ ትርጉሙን ግን አይቀይርም። ሆኖም ቃሉ በግሪክኛም ሆነ በአማርኛ የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። (የጥንት ግሪኮች ከመሬት በላይ ሦስት ደረጃዎች አሉ ብለው ያምኑ ነበር፦ ከባቢ አየር፥ ጠፈር፥ እና እግዚአብሔር የሚኖርበት ቦታ። በ2ኛ ቆሮንቶስ 12፡2-4 ላይ ያለው የጳውሎስ መልእክት ይህን አመለካከት ያንጸባርቃል።)

  በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ይህ ቃል ብዙውን ጊዜ "ሰማይ"፥ "ሰማያት"፤ አንዳንድ ጊዜም "መንግሥተ ሰማይ" ወይም "መንግሥተ ሰማያት"፤ አልፎ አልፎ ደግሞ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ተተርጉሟል። በዚህ ጉዳይ ላይ በ1954 ዓ.ም. የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ በ1980 ዓ.ም. ከታተመው በብዙ ይለያል።

በዚህ ጽሑፍ ላይ ነገሮችን ግልጥ ለማድረግ ሰንል፦

1. እግዚአብሔር የሚኖርበትን ቦታ ለማመልከት (አማኞች ከሞቱ በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን የሚሄዱበትን)፥ ወይም ከባቢ አየርን (ወፎች የሚበሩበትን)፥ ወይም ጠፈርን (ፕላኔቶችና ኮከቦች ያሉበትን) ቦታ ለመግለጥ "ሰማይ" ወይም "ሰማያት" በሚሉት ቃላት እንጠቀማለን።

2. በማቴዎስ ወንጌል ላይ ቃሉ ብዙ ጊዜ ከ"መንግሥት" ጋር በመቀናጀት "መንግሥተ ሰማያት" የሚል ጥምር ቃል ይፈጥራል። የያዘው ትርጉም ለየት ያለ ሲሆን፥ ይህም "በአሳታሚው ማብራሪያ" ላይ በዝርዝር ተብራርቷል።

የአሳታሚው ማብራሪያ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ‘‘የእግዚአብሔር መንግሥት’’ (አንዳንዴም ስለ ‘‘መንግሥተ ሰማያት’’) እናነባለን። ‘‘የእግዚአብሔር መንግሥት’’ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሦስት የተለያዩ አሳቦችን የሚገልጥ ነው፦

አንደኛው፥ በአጠቃላይ በዘመናቱ ሁሉ በሕያው ፍጥረታቱና በተፈጥሮ ላይ የሰማዩን ንጉሥ ግዛት ወይም አስተዳደር የሚያመለክት ነው። የዓለምን ጉዳይ ሁሉ የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ነው። ፈጥሮታል፥ ይጠብቀዋል፥ ፈቃዱንና እቅዱን ለማሟላት በተፈጥሮ እና በሰዎች (ጥሩና መጥፎ) ልብና ሕይወት ውስጥ ይሠራል። በአጭሩ፥ በዘመናት ሁሉ ያሉ ሰዎች ተቀበሉትም አልተቀበሉትም፥ ወደዱም ጠሉ፥ ወይም ተገነዘቡም አልተገነዘቡ፥ በሰማይ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥት ነው የሚኖሩት።

ይህ የእግዚአብሔር ግዛት አንዳንድ ጊዜ በአንዳንድ ቦታዎች ተቀባይነትና ድጋፍ የሚያገኝ ሲሆን፥ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ ውድቅ ይሆናል። ብዙ ጊዜና በብዙ ቦታዎች ሰዎች በእግዚአብሔር ግዛት ሥር መሆናቸውን አይገነዘቡም። ሆኖም፥ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፥ በውዴታም ሆነ በግዴታ ሁላችንም በእግዚአብሔር መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ነን።

ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለው ቃል እግዚአብሔርን የተቀበሉና ፈቃዱንም ለማድረግ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን በተለይ ለማመልከት በጥቅም ላይ ውሏል። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ ገዢያቸው የተቀበሉና ተገዢዎችም የሆኑ ናቸው። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ መንግሥት ነው፤ ማለትም የማይታይና የማይጨበጥ፥ በሰዎች ልብና አእምሮ ውስጥ ብቻ የሚገኝ ነው።

ሦስተኛ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ በምድር ላይ ይመሠረታል ተብሎ የተተነበየለትን ወደፊት የሚታይ ምድራዊ መንግሥት አንዳንዴ ያመለክታል። ይህ መንግሥት፥ ሰዎች እውነተኛ ንጉሥ በሆነው መሢሑ ኢየሱስ የሚመሩበት ነው። ምድራዊው መንግሥት ለእስራኤል ሕዝብ በአጠቃላይ (ዘፍጥ. 12፡1-6፤ 13፡14-17፤ 15፡18)፥ እና ለንጉሥ ዳዊት በተለይ (2ኛ ሳሙ. 7፡16) ተሰፋ ተሰጥቷል። ይህ መንግሥት ለ1000 ዓመታት ያህል ይቆያል ተብሎ ስለሚታመን፥ አንዳንዴ ‘‘የሺህ ዓመት መንግሥት’’ ተብሎ ይጠራል (ራእይ 20)።

አንድ ጠንቃቃ ተማሪ መጽሐፍ ቅዱስንም ሆነ ይህን ጽሑፍ በሚያነብበት ጊዜ ‘‘የእግዚአብሔር መንግሥት’’ የሚለው ቃል ቢያጋጥመው፥ በጸሐፊው አእምሮ ያለው ትርጉም የትኛው እንደሆነ መመርመር ያስፈልገዋል።

መቅድም

የኢየሱስ ምሳሌዎች፥ ቀላል በሆነ አቀራረብ ጥልቅ እውነቶች የተገለጡባቸው በመሆናቸው፥ የሃይማኖት መምህራንን ለረጅም ጊዜ ሲፈታተኑና ሰባኪያንን ሲያነሣሡ የኖሩ ናቸው። ቀላል የመምሰላቸው ነገር ግን ተርጓሚዎችን የሚያታልል ወጥመድ ሆኗል። ምሳሌዎቹን አስመልክቶ በቀረቡ ጽሑፎች ላይ የተደረገ ምርምር እንደሚያመለክተው፥ ብዙ ሰዎች ምሳሌዎቹን የተጠቀሙባቸው፥ የተጠቀሱበትን አገባብና የተነገሩበትን መነሻ ወይም ከቃሉ የሚወጣውን መልእክት በማጤን ሳይሆን፥ በአእምሯቸው ያሉ እውነቶችን ለማቅረቢያነት ነው። አንዳንድ ሰባኪያን ደግሞ ኢየሱስ ከተናገራቸው ቃላት ውስጥ እስከ ዛሬ ያልተደረሰበትን እውነት በማግኘት ረገድ ያላቸውን ክህሎት ጉባኤያቸው እንዲያምንላቸው ለማድረግ በመላምታዊ አተረጓጎም ተጠቅመዋል። የምሳሌዎቹ ቀዳሚ ዓላማ፥ መጀመሪያ ለተነገሩላቸው ሰዎች ለማስተማሪያነት ማገልገል እንደነበር ብዙ ጊዜ ይዘነጋል።

በዚህ አጭር መጽሐፍ፥ ጌታ ሊገልጥ የፈለገውን መሠረታዊ እውነት ለማግኘትና ለማቅረብ ይሞከራል። ይህ የሚደረገውም፥ ምሳሌዎቹ የተነገሩባቸውን አገባቦችና የተገለጡባቸውን መነሻዎች በማጥናት ነው። ምሳሌዎቹ በዋናነት የታለሙት ለማስተማሪያነት እንደመሆኑ፥ ትኩረት የሚሰጠው ከአጠቃቀማቸው ይልቅ በትምህርትነታቸው ላይ ይሆናል። ትክክለኛ አጠቃቀም የሚኖረው፥ በትክክለኛ አተረጓጎም ላይ ሲመሠረት ነው። የዚህ ጽሑፍ ደራሲ ዓላማ፥ ትምህርቶቹን በወጉ ለመረዳት ይቻል ዘንድ የክርስቶስን ቃላት መተርጎም ነው።

አንባቢው ምሳሌዎቹ ውስጥ ያለውን እውነት በግልጥ እንዲረዳና፦ ‘‘እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም’’ (ዮሐ. 7፡46)፥ የተባለለትን ጌታ ከልቡ እንዲያፈቅር የደራሲው ምኞት ነው።

መግቢያ

የንግግር ዘይቤዎች በየትኛውም ቋንቋ አሉ። ቋንቋውን ያስጌጡታል፥ ያበለጽጉታል። ለምሳሌ ፍቅረኞቹ፥ ፍቅራቸውን በበለጸገ ዘይቤያቸው ባይገልጡት ኑሮ፥ የሰለሞን መዝሙር ምንኛ የደበዘዘና ውበት አልባ ይሆን ነበር! ዘይቤዎች ቋንቋን ከማስዋብ ሌላም ተግባር አላቸው፥ ረቂቅ አሳብ ይገለጥባቸዋል። አሳብን ከሚታወቀው ወደማይታወቀው ዓለም በመቀየር፥ የማይታወቀው ዓለም እውነት በሚታወቀው አማካይነት ይገለጣል። ስለዚህ፥ የዘይቤዎች ቀዳሚ ተግባር አሳብን ማስተላለፍ ይሆናል። ዘይቤው ቀላልም ሆነ ውስብስብ መሠረታዊ ተግባሩ ይህ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ‘‘ምሳሌ’’ እየተባሉ የሚጠቀሱ ብዙና የተለያዩ ዘይቤዎች አሉ። ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን ‘ማሻል’ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል አንዳንዴ ‘‘ምሳሌ’’ ተብሎ ቢተረጎምም፥ በሌሎች አያሌ መንገዶችም አግልግሎት ላይ ውሏል። ከሞኝ ሞኝነት ጋር ሲነጻጸር (ምሳሌ 26፡7፥9)፥ መልካም ወይም ብልህ ምክር ምሳሌ ተብሏል (ዘኍል. 23፡18፤ ኢዮብ 27፡1፤ መዝ. 49፡4፤ 78፡2)። ትንቢታዊ መልእክትም እንዲሁ ምሳሌ ተብሏል (ዘኍል. 24፡15)። የፍርድ መልእክትም እንዲሁ ተገልጧል (ሚክ. 2፡4፤ እንባ. 2፡6)። ሕዝቅኤል መልእክት ያስተላለፈላቸው ሰዎች፥ ምክርና ማስጠንቀቂያውን አልተቀበሉትም። እንዲህ ብለውታል፦ ‘‘ይህ ምሳሌን የሚመስል አይደለምን?’’ (ሕዝ. 20፡49)። ብሉይ ኪዳን፥ ምሳሌ የሚለውን ቃል ለብዙ ትርጓሜዎች ቢጠቀምበትም፥ የእያንዳንዱ ቃል ማዕከላዊ ጉዳይ ግን፥ አሳብን ከተናጋሪው ወደ አድማጩ ማስተላለፍ ነው።

ምሳሌ የሚለው ቃል፥ በአዲስ ኪዳንም በብዙ የተለያዩ ክፍሎች በዘይቤያዊ አነጋገርነት አገልግሏል። እንዲሁም በንጽጽር ወይም ቅርፅ፥ አምሳያ ተብሎ እንደሚጠራው ሆኖ ሊቀርብም ይችላል። ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ ‘‘እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ’’ (ማቴ. 10፡16)። ‘‘እንደ’’ የሚለው ቃል በዚህ አገባቡ የንጽጽርን ዘይቤ ያመለክታል።

ምሳሌ ተመሳሳይነትን በሚጠቁም ተለዋጭ ዘይቤነት ቅርፅም ይቀርብ ይሆናል። ለምሳሌ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ ‘‘እኔ የበጎች በር ነኝ’’ (ዮሐ. 10፡7)።

ተመሳሳይነትን በቀጥታ በሚገልጥ መልክም ይቀርብ ይሆናል። በዚህ ዘይቤ፥ ማዘዋወሩ የሚከናወነው ከተራ እውቀት በመነሣት ነው።

የመሠረተው አንድ ሰው ባከናወነው ሳይሆን፥ በተደረገ ወይም ቀድሞ ባለ ነገር ላይ ነው። ክርስቶስ ‹‹መንግሥተ ሰማያት*፥ ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች›› (ማቴ. 13፡33) ሲል ተመሳሳይነትን ገላጭ በሆነ ዘይቤ መጠቀሙ ነበር። ከእንጀራ ወይም ዳቦ ጋገራ ጋር ግንኙነት ያለው ማንም ሰው፥ የጋገራው ሂደት የተለመደ ከመሆኑ የተነሣ፥ ከዘይቤው እውነትን ይማራል።

ምሳሌ፥ የታሪክ ወይም የትረካ መልክም ይይዝ ይሆናል። እውነትን፥ ተመሳሳይነትን በቀጥታ እንደሚገልጠው ዘይቤ ሰዎች ወደሚያደርጉት ጠቅላላ ነገር የሚያዛውር አይደለም። ትረካ ወይም ታሪካዊ ምሳሌ ግልጥ ነው፤ የታወቀ ድርጊትን የሚመለከተውን እውነት ይለውጥና አሳብ ወደ አንድ ሰው ድርጊት እንዲያመራ ያደርጋል። ኢየሱስ ይህን የመሰሉ ሦስት ምሳሌዎች ቀጥሎ ባለው አኳኋን ገልጧል፦ ‹‹አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት›› (ሉቃስ 15፡11)፥ ‹‹አንድ ባለጠጋ ሰው ነበር›› (ሉቃስ 16፡1)፥ ‹‹በአንዲት ከተማ... አንድ ዳኛ ነበር›› (ሉቃስ 18፡2)። ለአድማጮቹ እውነትን ለማስተማሪያነት ብዙ ጊዜ የተጠቀመው በታሪካዊ ምሳሌ ዘይቤ ነው። ምሳሌያዊ አነጋገሮች ተለዋጭ ወይም ተዘዋዋሪነትን ስለሚያስተምሩ፥ አንዳንድ ጊዜ ምሳሌ ይባላሉ (ለአብነት፥ ሉቃስ 6፡39)። ሉቃስ 4፡23 ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገር ‹‹ምሳሌ›› ተብሏል። የምሳሌያዊ አነጋገር መሠረታዊ ትርጉም አጠቃቀሞች ‹‹ትምህርት›› (ማቴ. 24፡32፤ ማር. 13፡28)፥ ‹‹ገለጣ›› (ዕብ. 9፡9)፥ እና ‹‹ዘይቤያዊ አነጋገር›› (11፡19) ናቸው።

ታሪካዊ ምሳሌን ብሉይ ኪዳን ውስጥም እናገኛለን። ነቢዩ ናታን ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ለሠራው ኃጢአት ቅጣት ወይም ፍርድ ለማስተላለፍ፥ የዳዊትን ኃጢአት በታሪካዊ ምሳሌ ውስጥ በማቀናበር ነው የተጠቀመው (2ኛ ሳሙ. 12፡1-4)። ይህ ታሪካዊ ምሳሌ ከጌታችን ምሳሌዎች የብዙዎቹን ቅርፅ ቀድሞ ያመለከተ ነበር።

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች ቢለያዩ፥ በትምህርት የሚያስጨብጡት እውነት ከነባራዊው እውነታ የሚነሣ ወይም የሚወሰድ ከመሆኑ አንጻር ተመሳሳይነት አላቸው። ይዘቱና ሁልጊዜ ለመሆን የመቻሉ ነገር የተለመደ ነው።

---

* በዚህ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ አሳብ ለማግኘት በጽሑፉ መጀመሪያ ‹‹ማሳሰቢያ›› በሚል ርእስ ሥር የቀረበውን ይመልከቱ።

በምሳሌያዊ አገላለጥ፥ ካልታወቀው ዓለም ወደ ሌላ ያልታወቀ ዓለም ለመሸጋገር ሙከራ አልተደረገም፤ ሽግግሩ ሁልጊዜ ከታወቀው ወዳልታወቀው ዓለም ነው።

በእንቆቅልሽ (Allegory/አሊጎሪ) ወይም ግልጥ ከሆነው ፍች ባሻገር፥ ሌላ ትርጓሜ ያለው ቃል የሚገለጠው ታሪክ፥ በምሳሌ እንደሚገለጠው በእውነታ ላይ የሚመሠረት አይደለም። ስለዚህ በእንቅልሽ አማካይነት የሚተላለፍ መልእክት፥ በተጨባጭ እውነታ ላይ ሳይሆን፥ በአድማጩ ምናባዊ አጠቃቀም ላይ ነው የሚመሠረተው። በእንቆቅልሽ የሚተላለፉ መልእክቶችን የሚያስገነዝቡ ብዙ ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ። ሕዝቅኤል፦ "በእንቆቅልሽ አጫውት፥ ለእስራኤልም ቤት ምሳሌ ንገር" (ሕዝ. 17፡1) በመባል ታዞ ነበር። ነቢዩ፥ የኢየሩሳሌምን በናቡከደናጾር መወረርና የሕዝቡን ወደ ባቢሎን በምርኮ መወሰድ ለማስታወስ ፈለገ። ይህን ያደረገው፥ የዝግባ ጫፍ ሰብሮ ወደ ሌላ ቦታ በመውሰድ በአዲስ መሬት የተከለ ንሥርን ታሪክ በእንቆቅልሽ በማቀናበር ነበር። ይህ ትረካ ከተለመደው ተፈጥሯዊ ሁኔታ የሚቃረን ስለሆነ እንቆቅልሽ ነው። በታሪኩ ውስጥ ንሥሮች በተለምዶ የማያደርጉትን ያደርጋሉ። ታዲያ ሕዝቡ እንቆቅልሹን ይረዳ ዘንድ ነቢዩ የመልእክቱን ምሥጢር መፍታት ነበረበት። ሌላው እንቆቅልሻዊ ገለጣ መሳፍንት 9 ውስጥ ይገኛል። የሴኬም ሰዎች አብሜሌክን ንጉሣቸው አድርገውት ነበር። ኢዮአታም ይህን ድርጊት በሰማ ጊዜ በእንቆቅልሽ ነቀፋቸው። እንቆቅልሹን የጀመረው የጫካ ዛፎችን ንጉሥ የሚሹ አድርጎ በማቅረብ ነው። ዛፎች የወይራ ዛፍን ንጉሣቸው እንዲሆን ቢጠይቁት እምቢ አላቸው። የበለስ ዛፍን ጠየቁት፥ እርሱም እምቢ አላቸው። ወይንንም ጠየቁት እርሱም እንዲሁ። በመጨረሻም ወደ እሾህ ሄዱና ንጉሣቸው እንዲሆን ጠየቁት። እሾሁም ዛፎቹ ለርሱ ሥልጣን የሚገዙበትን ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ጥያቄያቸውን ተቀበለ። ኢዮአታም በእንቆቅልሹ የገለጠው፥ የሴኬም ሰዎች ንጉሣቸው እንዲሆን ከመካከላቸው የመረጡት እጅግ ያነሰውን ሰው መሆኑን በማመልከት ነበር። ይህ ታሪክ በእውነታ ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ እንቆቅልሽ ነው። ከተፈጥሮ ጋርም ተቃራኒ ነው፤ ዛፎች በታሪኩ ላይ ያነበብነውን ነገር አያደርጉምና።

በዚህ መሠረት፥ እውነት የተገለጠው ከሚታወቀው ዓለም ወደማይታወቀው በሚሸጋገር እንቆቅልሽ አይደለም። በእንቆቅልሽ (አሊጎሪ) አማካይነት እውነትን የመረዳቱ ጉዳይ፥ ከሚታወቀው ወደማይታወቀው በማሸጋገሩ ላይ ሳይሆን፥ በአድማጩ የግንዛቤ ብቃት ላይ

በመመሥረት ነው። እንቆቅልሽ እውነትን ለማስተማር በእያንዳንዱ ክፍል ራሱን ችሎ ይቀናበራል። በመሆኑም ይህ ሁኔታ የእንቆቅልሽ ፈቺ ወይም ተርጓሚ የሆነ ሰው፥ እያንዳንዱን ዝርዝር ሁኔታ በጥንቃቄ እንዲመለከት ያደርገዋል። በተቃራኒው የምሳሌ ዓላማ አንድ አስፈላጊ እውነትን ማስተማር ሲሆን፥ የምሳሌ ዝርዝርም እንዲሁ አጋጣሚ ይሆን ይሆናል። ክርስቶስ እንቆቅልሽን እንደ ዘይቤ ለእውነት መግለጫነት እንዳልተጠቀመበት ልብ እንበል።

ክርስቶስ በምሳሌዎች የተጠቀመበት ዘዴ

ክርስቶስ በአገልግሎቱ ወቅት ሁሉ በሚናገራቸው ቃላት ጠቀሜታ ላይ ልዩ ትኩረት አሳርፎባቸዋል። ቃላቱ፥ ካደረጋቸው ተአምራት ጋር ተዳምረው የማንነቱን ዋና ማረጋገጫ አጉልተውታል (ዮሐ. 8፡28፤ 14፡10)። በወንጌላት በተመዘገበው መሠረት፥ ከክርስቶስ አስተምህሮዎች ከሦስት አንዱ እጅ በምሳሌ መልክ የቀረበ ነበር። ከዚህ በመነሣት ለምንድነው ክርስቶስ ይህን ዘዴ እውነትን ለማስተላለፊያነት የተጠቀመበት? የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት።

ለትምህርቱ ማስተላለፊያነት በምሳሌዎች የተጠቀመበትን ምክንያት ክርስቶስ ራሱ ገልጦታል (ማቴ. 13፡10-17)። ይህን ያለው የዘሪውን፥ የዘሩንና የመሬቱን ምሳሌ ከተናገረ በኋላ ነው። ደቀ መዛሙርቱ "ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ?" (ቁ. 10) በማለት ጠየቁት። ጥያቄያቸው የሚያመለክተው፥ ክርስቶስ አዲስ የማስተማሪያ ዘዴ መጠቀም እንደጀመረ መረዳታቸውን ነው። ቀደም ባለው አገልግሎቱ ሂደት እንደ ኋለኛው ባይሆንም በምሳሌዎች ተጠቅሞ ነበር። ከዚህ አኳያ ሲታይ የደቀ መዛሙርቱ ጥያቄ ትኩረት የሚስብ ይሆናል። በታሪካዊ ምሳሌ የሚጠቀምበትን ሁኔታ እንዲህ ሲል ገልጿል፦ "ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቷችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም፥ ላለው ይሰጠዋልና፥ ይበዛለትማል፤ ከሌለው ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። ስለዚህ እያዩ ስለማያዩ እየሰሙ ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸዋለሁ። መስማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም" (ማቴ. 13፡11-14)። ክርስቶስ በምሳሌ የማስተማር ዘዴ የተጠቀመው በአንድ በኩል እውነትን ለጥቂቶች ለመግለጥ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ግን እውነትን ከሌሎቹ ለመሸሸጊያነት መሆኑን ገልጿል። የተለያዩ አድማጮች ነበሩ ትምህርቱን የሚሰሙት፤ ግማሾቹ አማኞች፥ ሌሎች የማያምኑ ነበሩ። ግማሾቹ በርሱና

በስጦታው ሲያምኑ፥ ሌሎቹ ግን እንደ መሢሕ ሊቀበሉት አልፈቀዱም። ሁለቱን ወገኖች መለየቱ አይቻልም። ስለሆነም ክርስቶስ አማኞችን ሊያስተምር ፈለገ። ይህን ሲያደርግ ግን፥ ለማያምኑት በኃላፊነት የሚጠየቁበትን እውነት በመንገር የበለጠ ጫና ሊያኖርባቸው አልፈለገም።

መጥምቁ ዮሐንስ መሢሑን ለቃል ኪዳን ሕዝቦች ለማስተዋወቅ የተገለጠ አገልጋይ ነበር። ሕዝቡ ንስሐ እንዲገቡና መሢሑን ተቀብለው ወደ መንግሥቱ ለመግባት እንዲዘጋጁ አሳሰባቸው። የንስሐቸው ፍጹምነት በጽድቃቸው ፍሬ ሊታይ እንደሚገባም አስገነዘባቸው። እርሱ የአዋጅ ነጋሪነቱን ወይም የማስተዋወቅ አገልግሎቱን እንዳበቃም፥ ክርስቶስ ለሚጠብቁት ሕዝቦች ራሱን በግልጥ እንደ መሢሕ አቀረበ (ማቴ. 4፡17)። ራሱን እንደ መሢሕ መስጠቱን አጸናላቸው። የቃል ኪዳኑን መንግሥት ያመጣ መሆኑንም ይፈጽማቸው በነበሩ ተአምራት አረጋገጠላቸው። ከማቴዎስ 8-11 ያሉት ክፍሎች ክርስቶስ ለሕዝቡ እንደማረጋገጫ ከሰጣቸው ተአምራት ጥቂቱን መዝግበዋል። በዚህ ጊዜ ክርስቶስ የተና ራቸው ምሳሌዎች ጥቂት ነበሩ።

ምድራዊ ሕይወቱ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰው ማቴዎስ 12 ላይ ነው። በዚህ ስፍራ ክርስቶስ ዲያብሎስ አድሮበት ዕውርና ድዳ የነበረን በመፈወሱ ሰዎች፥ "ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን?" (ቁ. 23) እያሉ በመጠየቅ እንደ ልዑልና አዳኝ ሊቀበሉት መፍቀዳቸውን ገለጡ። በግሪክኛው አገባብ ጥያቄው የሚጠብቀው መልስ አሉታ ነው። ያም ሆነ ይህ የሕዝቡ መሪዎች ቢፈቅዱ ኑሮ፥ ክርስቶስ ስለ ራሱ ያቀረበው ማስረጃ

---

* "ፈሪሳውያን። ከአይሁድ የሃይማኖት ወገኖች አንዱ ክፍል። እነርሱም የሙሴን ሕግ በብዙ ጥንቃቄ ተረጎሙ። ሰዎች ሕጉን እንዳይተላለፉ ብዙ ትእዛዝና ሥርዓት ጨመሩበት። ይህም ለተራው ሕዝብ ከባድ ሸክም ሆነ (ማቴ. 15፡1-4፤ 23፡1-4)። ዋና አሳባቸው ሰው የሚጸድቀው በግል ሕይወቱና ሕግን በመፈጸም ነው የሚል ነበር (ሐዋ. 15፡5)። በመካከላቸው እንደነኒቆዲሞስና እንደነጻውሎስ ያሉ ቅን ሰዎች ነበሩ። ብዙዎች ግን በሕግ ላይ የተጨመረውን የአባቶች ወግ እየተመለከቱ ዋናውን የሕግ መንፈስ፥ ፍርድን፥ ምሕረትን፥ ታማኝነትንም ረሱ። በዚህ ምክንያት ክርስቶስ ደጋግሞ ግብዞች በማለት ወቀሳቸው (ሉቃስ 11፡37-44፤ ማቴ. 23)። በክርስቶስ ጊዜ ፈሪሳውያን ስድስት ሺህ ያህል ነበሩ። ፈሪሳውያንን የተቃወሙ በቤተ መቅደስም ሥልጣን ያገኙ ሰዱቃውያን ነበሩ (ሐዋ. 23፡6-8)። ፈሪሳውያን ክርስቶስን ለመግደል ተማከሩ (ዮሐ. 11፡47-57)። በኋላም አንዳንዶች በክርስቶስ አመኑ (ሐዋ. 15፡5)" (የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፥ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፥ 1972)።

ሕዝቡ እንደ መሢሕ እንዲቀበሉት የሚያስችላቸውና በቂ ነበር። ፈሪሳውያን* ስለ ክርስቶስ የነበራቸው አመለካከት እንዲህ የተዛባ በመሆኑ ሌላ ገለጣ ሰጡ። ክርስቶስ ኃይል የተቀበለው ከአባቱ መሆኑንና ከእግዚአብሔር የተላከ መሢሕ መሆኑን በመካድ፥ ኃይል የተቀበለው ከሰይጣን ስለሆነ የእስራኤል መሢሕ ሊሆን አይችልም አሉ። የእስራኤል መሪዎች በጊዜው ያሳዩት አለማመን፥ በመስቀል ሞት ሊደመደም ያለውንና ሕዝቡ በክርስቶስ ላይ የሚኖረውን የኋላ ዓመፅ ያመለክት ነበር።

ክርስቶስ ኃይል የተቀበለው ከሰይጣን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ሦስት ማስረጃዎች አቅርቧል (ቁ. 25-29)። ሕዝቡ የፈሪሳውያንን አባባል ወይም ትርጉም በማመን ከጸኑ፥ የከፋ ፍርድ የሚደርስባቸው መሆኑን በጥብቅ አስጠነቀቃቸው (ቁ. 30-32)። ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ክርስቶስ ከሰይጣን አለመሆኑን ያምኑ ዘንድ ከሰማይ* የመጣ መሆኑን እንዲያረጋግጥላቸው ጠየቁት። የርሱ መልስ የዮናስን ምልክት መስጠት ነበር። የክርስቶስ ትንሣኤ ሰይጣን አስመስሎ ሊሠራ የማይቻለው አንድ ምልክት ነበር። በመሆኑም ይህ ራሱ የክርስቶስን የእስራኤል መሢሕነት ያረጋግጣል። ከፈሪሳውያን ጋር የነበረው ግጭት ዘገባ፥ የክርስቶስ እናትና ወንድሞች በስብሰባው ዳር ሆነው ሊያናግሩት መሻታቸውን ከሚገልጠው ጋር ይቀራረባል። ይህ የቤተሰቦች ጥያቄ በሥጋዊ ዝምድና ላይ የተመሠረተ ስለነበር ክርስቶስ ችላ አለው። ከሱ ጋር ያላቸው ግንኙነት የሥጋ ዝምድና ሲሆን፥ የጊዜው የክርስቶስ ዓላማ ግን፥ ከእምነት የሚመጣ መንፈሳዊ ዝምድና የሚያስፈልግ መሆኑን ማሳየት ነበር። ስለሆነም በሥጋ እንዛመድሃለን የሚሉትን አልተቀበላቸውም። ‘‘እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ፦ እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፤ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ፥ እኅቴም እናቴም ነውና አለ’’ (ቁ. 49-50)። በዚህ አኳኋን ሕዝቡ ክርስቶስን ወዳለመቀበሉና፥ በመጨረሻም ድምፁን ከፍ አድርጎ እንዲሞት ወደመፍረዱ እንደሚያዘነብል በማቴዎስ 12 ውስጥ ተመልክቶ ነበር። ክርስቶስም በበኩሉ ሕዝቡን ገለል እንደሚያደርግና መንግሥቱንም ከዚያ ትውልድ የሚወስድ መሆኑን ገልጧል። የዳዊት ዙፋን አምሳያ የነበረው መለኮታዊ አገዛዝ (Theocracy) ክርስቶስ ወደፊት በክብርና በኃይል ወደሚገለጥበት ጊዜ ተላለፈ።

የዳዊት መለኮታዊ አገዛዝ መተላለፍ ማጠቃለያ የሚገልጠው፥ ክርስቶስ የዚያን መንግሥት ዕቅድ እውነት በርሱ ላመኑትና የርሱ ለሆኑት

* በጽሑፉ መጀመሪያ ላይ የሚገኘውን ማሳሰቢያ ይመልከቱ።

ለማሳወቅ የፈለገበትን ምክንያት ነው። እርሱ በዘይቤያዊ አነጋገር ባይጠቀም ኑሮ፥ ያመኑም ሆኑ ያላመኑት እርሱ ያለውን በቀላሉ ይረዱ ነበር። የማያምኑት ተረድተው ባለማመናቸው በላያቸው የከፋ ፍርድ አምጥተዋል። ለዚህ ነው ክርስቶስ ምሳሌያዊ የማስተማር ዘዴ የመረጠው። ምሳሌ በመጠቀም ከማያምኑት እውነትን ሸሸገባቸው። ይህን ያደረገው የአዋቂ አጥፊ በመሆን ወደ ፍርድ ወይም ወደ ኃላፊነት እንዳይገቡና ነጻ እንዲሆኑ በማሰብ ነበር። በዚህ አሠራሩም እውነትን ለአማኞች አስተላልፏል።

ከዚህ አኳያ ነበር ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ ብዙዎቹን ምሳሌዎች የተናገራቸው። በሕዝቡ ክርስቶስን አልቀበልም ማለትና፥ በስቅለቱ መካከል የታወቁ ተአምራት ቢደረጉም፥ የተአምራቱ ዓላማ የኢየሱስን መሢሕነት ለሕዝቡ ማሳመን አልነበረም። ዋና ጉዳያቸው ከእስራኤል ግትር እምቢ ባይነት አኳያ ነው መታየት ያለበት። ተአምራቱ ከክርስቶስ ቃልና ተግባራት ይማሩ ለነበሩ አማኞች እውነትን ለመግለጥ የታቀዱ ነበሩ።

የምሳሌዎች አተረጓጎም

ክርስቶስ እውነትን በማስተማር ላይ ያተኮሩ ምሳሌዎቹን በተናገረ ጊዜ፥ አማኞች ምሳሌዎቹን እንዲረዱ፥ ከምሳሌዎቹም ትርጓሜ እንዲያወጡና ሊገልጥ የፈለገውን እውነት እንዲገነዘቡለት ይፈልግ ነበር። የአይሁድ መሪዎች የክርስቶስን መሢሕነት አለመቀበላቸውን ካሳወቁ በኋላ፥ ከተነገሩት ምሳሌዎች ሁሉ (ማቴ. 12) በክርስቶስ የተተረጎሙት ሁለቱ ብቻ መሆናቸውን መረዳቱ ትኩረት የሚሰብ ጉዳይ ነው። እነሱም የዘሪው፥ የዘሩ፥ የመሬቱና የአረሙ ምሳሌዎች ናቸው። ይህ እውነትን የማስተላለፊያ አዲስ መንገድ እንደመሆኑ፥ ለምሳሌዎቹ መፍቻ እንደ ዓይነት ይሆኑ ዘንድ ለእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ትርጓሜ ሰጠ። የኋለኞቹን ተከታታይ ምሳሌዎች አለመተርጎሙ የሚያመለክተው፥ አድማጮቹ ምሳሌውን ሙሉ በሙሉ እንዲረዱ መፈለጉን ነው። ይህ ጉዳይ ክርስቶስ በምሳሌዎች አማካይነት ሊያስተላልፍ ስለፈለጋቸው እውነቶችና ለነሱም የተሰጧቸውን ስሞች አስመልክቶ አሁን ካለው ግራ መጋባት አኳያ ሲታይ፥ ትኩረት የሚሰብ ይሆናል።

ምሳሌዎቹን በአግባቡ ለመተርጎም የሚሻ ሰው አንዳንድ መመሪያዎችን መከተል አለበት። የመጀመሪያውና ጌታ ራሱ የገለጠው

መመሪያ፥ ምሳሌዎች፥ ‘‘መንግሥተ ሰማያትን’’ (ማቴ. 13፡11) የሚመለከቱ መሆናቸው ነው። መንግሥተ ሰማያት ኃያሉ እግዚአብሔር የሚገዛበት ስፍራ ነው። እግዚአብሔር ልዑል ወይም ሁሉን አድራጊ እንደመሆኑ፥ መለኮታዊ አገዛዙን በተመለከተ የሥልጣን ውክልና ሊሰጥ ይችላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን መለኮታዊ አገዛዙ በተለያዩ ሁኔታዎች ተመርቷል። አዳም በገነት በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ ገዝቶታል ወይም አስተዳድሮታል። አገዛዙን በእግዚአብሔር ስም እንዲለማመድም ለአዳም ሥልጣን ሰጥቶት ነበር። ከአዳም መውደቅ በኋላ፥ እግዚአብሔር ሕግጋቱ በሰዎች ልብ የተጻፉ መሆናቸውን በሚያረጋግጠው ሕሊና አማካይነት (ሮሜ 2፡15) በተዘዋዋሪ ገዝቷል። ከጥፋት ውኃ በኋላ ደግሞ የገዛው በሰብአዊ መንግሥታት አማካይነት ነው። ይህን ያደርግ የነበረው፥ ገዥዎች ሕግና ሥርዓት እንዲያከብሩ በማዘዝና፥ ጻድቃን በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ በመፍጠር ነበር። ድርጊቱ አንዳንዴ ሕግ የሌላቸውን ሰዎች ሞት ቢያስከትልም፥ የእግዚአብሔርን ሥልጣን በሥራ ላይ ማዋል የመንግሥት አስተዳዳሪዎች ኃላፊነት ነበር (ሮሜ 13፡1-7)።

አብርሃምን ሲጠራው፥ እቅዱ ከአብርሃም አብራክ በሚወጣውና በዓለም በሚሰፋው ሕዝብ አማካይነት መለኮታዊ አገዛዙ እንዲስፋፋ ነበር። እንዲሁም የአባቶች አለቆች፥ መሳፍንት፥ ነገሥታትና ነቢያት የመንግሥቱ አስተዳዳሪዎች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል። በዚህ ጊዜ የመጨረሻው መለኮታዊ መንግሥት አስተዳዳሪ ወይም ገዥ ከዳዊት ቤት እንደሚወጣና፥ በዳዊት ዙፋን ላይ ሆኖ መንግሥቱን እንደሚመራ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል (2ኛ ሳሙ. 7፡16)። እንዲህ ነበር የቃል ኪዳኑ ሕዝቦች የሺሁ ዓመት መንግሥት፥ የመጨረሻው መለኮታዊ መንግሥት እንደሆነ ቆጥረው ይጠብቁ የነበረው። ይሁን እንጂ፥ ሕዝቡ መሢሑ መንግሥቱን በመመሥረት፥ ቃል ኪዳኑን ለመፈጸም ራሱን በሚሰጣቸው ጊዜ ክደው ሞት የሚፈርዱበት መሆኑ በብሉይ ኪዳን በግልጥ አልተጻፈም። መሢሑ ተቀባይነት በማጣቱ የዳዊት ዙፋን አምሳያ የነበረው መለኮታዊ አገዛዝ መተላለፍ ነበረበት።

የእግዚአብሔር እቅድ፥ በእስራኤል በአሁኑ ዘመን መሢሑን መካድና ወደፊት መቀበል መካከል አዲስ መለኮታዊ አገዛዝ እንዲገለጥ ነበር። ይህ አዲስ አገዛዝ የመጨረሻው መለኮታዊ አገዛዝ ሳይሆን፥ መካከለኛው ነው። ክርስቶስ በማቴዎስ 13፡11 ‘‘የመንግሥተ ሰማያት ምሥጢር’’ ሲል፥ በብሉይ ኪዳን ስላልታየውና በርሱ ትምህርት ስለሚገለጠው መለኮታዊው አገዛዝ አዲስ ገጽታ መናገሩ ነበር። በምሳሌ

የቀረበው ትምህርት አብዛኛው ክፍል የሚመለከተውም ስለ አዲሱ መለኮታዊ መንግሥት ማለት፥ ስለ መንግሥተ ሰማያት መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል። ብዙዎቹ የጌታ ምሳሌዎች እንዲህ በሚሉ ቃላት ይጀምራሉ፦ ‘‘መንግሥተ ሰማያት ...ትመስላለች’’ (ማቴ. 13፡24፥ 31 እና ሌሎችም)። ይህ የሚያመለክተው፥ የመለኮታዊው መንግሥት ዕቅድ በምሳሌዎቹ በዋናነት ይታይ እንደነበር ነው። ቤተ ክርስቲያን የመለኮታዊው መንግሥት አካል ከመሆኗና ዕቅዱም በምሳሌዎቹ በተገለጡት ጊዜያት ክልል የተሰፋፋ ከመሆኑ የተነሣ፥ ብዙ ተርጓሚዎች ምሳሌዎቹ ለቤተ ክርስቲያን የተነገሩ አስመስለው በስሕተት አቅርበዋል (በዋናነት ለቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አስመስለው)። ይሁን እንጂ ምሳሌዎቹ የተነገሩት ሰፋና ጠለቅ ያለውን የመለኮታዊ አገዛዝ ዕቅድ ለመግለጥ መሆኑን ማስታወስ ይኖርብናል።

ሁለተኛውና ጠቃሚው የትርጓሜ መመሪያ፥ በቅርቡ ያለውን ዓረፍተ ነገር አገባብ መመልከት ነው። ምሳሌዎች ያለ ምክንያት አልተነገሩም። ክርስቶስ አንድ ምሳሌ በተናገረበት አጋጣሚ ሁሉ አድማጮቹ የገጠማቸውን አንድ ችግር ወይም ጥያቄ ይገልጥ ነበር። ለምሳሌ ስለማይታክተው ወዳጅ የተነገረው ምሳሌ (ሉቃስ 11፡5-7)፥ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ‘‘እንጸልይ ዘንድ አስተምረን’’ (ቁ. 1) በማለት ላቀረበለት ጥያቄ ክርስቶስ የሰጠው መልስ ነበር። ጌታ የባለጠጋውንና የአልአዛርን ምሳሌ (ሉቃስ 16፡19-31) የተናገረበት ምክንያት ቀጥሎ ያለው ነው፦ ‘‘ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ...ያፌዙበት ነበር’’ (ቁ. 14)። ይህ መመሪያ፥ ችግሩ ወይም ጥያቄው ቢገለጥም ሆነ ውስጠ ታዋቂ ቢሆን፥ ወይም በክርስቶስ ብቻ ቢታወቅ፥ ለሁሉም ምሳሌዎች ያገለግላል። ስለዚህ ምሳሌውን የሚተረጉመው ሰው፥ ክርስቶስ ራሱ የሚናገርለትን ችግር ወይም ጥያቄ ለመለየት ይቻለው ዘንድ፥ በገለጣው አቅራቢያ ያለውን የዓረፍተ ነገር አገባብ መመርመር አለበት። ይህ ሲታወቅ፥ ተርጓሚው ፍቺ በመስጠት ተግባሩ ሊቀጥል ይችላል። ይህ አሠራር ለችግሩ መፍትሔ ይሰጣል። መልሱ ከችግሩ ወይም ከጥያቄው የማይስማማ ከሆነ፥ ተርጓሚው፥ ወይ ጥያቄው አልገባውም ወይም ምሳሌውን በአግባቡ አልተረጎመውም።

ይህ መመሪያ በትርጉሙ ላይ ገደብ ያደርግበታል። በትርጉም ጊዜ በራስ ብልሃት ከመመራት ይከለክላል፥ በአሳብ ከመጋለብም ያግዳል። ለመሠረታዊው ጥያቄ ወይም ችግር መልስ ለሚሰጠው ምሳሌ አንድ ክፍል ሊተረጎምና አስፈላጊ ያልሆኑ ወይም ለመፍትሔው ምንም ድርሻ

የሌላቸው አሳቦች እንዲቀሩ ለማድረግ ምሳሌው ተተርጉሞ እስኪያበቃ ድረስ ችግሩ ወይም ጥያቄው ግልጥ የማይሆንበት አንዳንድ አጋጣሚዎች ይኖሩ ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ ተርጓሚው ወይም ፈቺው የጽሑፉን አገባብ በመመርመር፥ ምሳሌው እንዲነሣ ያደረገውን ችግር ወይም ጥያቄ የሚጠቁሙ ምልክቶች ሊያገኝ ይችላል።

አንድ ሰው የጽሑፉን ሰፊ አገባብ ከተገነዘበ በኋላ፥ የምሳሌው ትርጉም ቅርብ ካለው አገባብ አኳያ ሲታይ የተወሰነ ከሆነበት፥ ምሳሌውን ራሱ መተርጎም ይችላል። ይህ አሠራር ጠቃሚ ወደሆነው ሦስተኛ መመሪያ ይወስዳል፤ ይኸውም በተነሣው አሳብ ውስጥ ያለውን ጉዳይ ለማወቅ ምሳሌው መጠናት አለበት የሚል ነው። ለምሳሌ ስለማትታከተው መበለት በተነገረው ምሳሌ (ሉቃስ 18፥1-8)፥ የታሪኩ ትኩረት፥ በዳኛው ባሕርይ ላይ ሳይሆን፥ በመበለቲቱ አለመታከት ላይ ነው። ትኩረት የተሰጠው ለዳኛው ባሕርይ ቢሆን ኑሮ፥ ምሳሌው የተተረጎመው ያለ አግባብ ይሆን ነበር። ስለዚህ በምሳሌው ውስጥ ያለውን ዋና ጉዳይ ከብዙ ዝርዝሮች ለይተን ማውጣት አለብን።

አራተኛ መመሪያም አለ። ምሳሌ እውነትን ከሚታወቀው ዓለም ወደማይታወቀው የሚያሸጋግር እንደመሆኑ፥ ተርጓሚው ምሳሌው ውስጥ ያለውንና እውነት የሚተላለፍበትን ተጠቃሽ ነገር ማጥናት አለበት። ስለ አዘራር በሚገባ ያልተረዳ ሰው፥ የዘሪውን ምሳሌ ሊፈታ ወይም ሊተረጉም አይችልም። እንዲሁም በክርስቶስ ዘመን ስለነበረው የወይን ጠጅ አጠማመቅ በሚገባ ያልተረዳ ሰው፥ ስለ አዲስ ወይንና አሮጌ አቁማዳ የተነገረውን ምሳሌ ሊረዳ አይችልም። ባህላችንን ክርስቶስ በነበረበት ጊዜ ባለ ሁኔታ ላይ በመጫን በአንድ ምሳሌ ውስጥ ያለን እውነት ለማግኘት አንችልም። ስለዚህ ምሳሌዎችን የሚያጠና ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረውን ታሪክ፥ መልክዓ-ምድር፥ ባህልና ልማድ መመርመር አለበት። በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎችን አስተሳሰብ መማርን መልመድ አለበት። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ አውደ ጥበብ (Encyclopedia/ኢንሳይክሎፒዲያ) ወይም የመጽሐፍ ቅዱስን ባህል አስመልክቶ የተጻፉ መጻሕፍት፥ ምሳሌዎችን ለመተርጎም የሚጠቅሙና ምትክ የለሽ መሣሪያዎች ናቸው። ምሳሌዎችን በመተርጎም ረገድ በጊዜያችን የሚገጥመን ችግር፥ ምሳሌዎቹ የተነገሩበትን ተጠቃሽ ሥርዓት ወይም ክልል መረዳቱ ነው። ምሳሌውን ለመረዳት ከመሞከራችን በፊት እነዚህ ሁኔታዎች በግልጥ መታየት አለባቸው። ክርስቶስ ምሳሌዎቹን ሲናገር የሰሙት፥ በዚያ ባህል ውስጥ የኖሩና

የሚያውቁት ስለሆኑ ይህ ችግር አልነበረባቸውም። ጌታም የምሳሌው መሠረት ያደረጋቸውንና የተናገረባቸውን ነገሮች መግለጡ አላስፈለገውም ነበር። ጥሩ ተርጓሚዎች እንሆን ዘንድ፥ ክርስቶስን እንዳዳመጡት ሰዎች ስለ ፍልስጥኤም ባህል፥ ልምድና ዕለታዊ ሕይወት እውቀት ሊኖረን ይገባል።

ይህ እውቀት ያለው አንድ ሰው ምሳሌዎችን ለመተርጎም ይችላል። ተርጓሚው ሕንጻንና የበርን አገልግሎት ከማወቁ አንጻር ክርስቶስ ‘‘እኔ...በር ነኝ’’ (ዮሐ. 10፡7) ሲል ምን ማለቱ እንደሆን ይረዳል። ክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር መግቢያ መሆኑንና በርሱ በኩል ለሚመጡትም ሰላምና ደኅንነት የሚሰጣቸው መሆኑን እንደገለጠ ተርጓሚው ያውቃል። ወደ ደኅንነቱ የሚገቡ ሁሉ የመግባትና የመውጣት ነጻነት እንደሚኖራቸውም ይረዳል። የእረኛን ተግባር በሚገባ የሚያውቅ ሰው ‘‘መልካም እረኛ እኔ ነኝ’’ (ቁ. 14) ከሚለው የክርስቶስ ንግግር ይህን ይረዳል። ክርስቶስ የሚገልጠው፥ አማኞች የርሱ መሆናቸውን፥ እንደሚመራቸው፥ እንደሚጠብቃቸው፥ እንደሚመግባቸውና የሚያስፈልጋቸውን እንደሚሰጣቸው ነበር። ከዚህ የምንረዳው ነገር፥ አንድ ሰው እንዲህ ያለውን አስተምህሮ በዘይቤ ከመለየቱ በፊት የቃሉ ዘይቤ እውቀት ሊኖረው የሚገባ መሆኑን ነው። ከምሳሌ የሚገኘው የቃል በቃል እውነት ትምህርት፥ በምሳሌው ውስጥ ባለ ሥረ-ታሪክ ወይም መነሻ ትርጓሜ ይወሰናል። በዘይቤ ለመጠቀም ቃል በቃል ያልሆነ ወይም ዘይቤያዊ ትርጉም የግድ አያስፈልግም። ዘይቤያዊ ቋንቋ ከዚያ ይልቅ የሚጠይቀው (የዘይቤው ትርጉም እርግጠኛ እንዲሆን ከተፈለገ)፥ ከታወቀው ዓለም ወዳልታወቀው የሚደረግን የቃል በቃል ትርጉም ነው።

እነዚህን ቀላል፥ ግን አስፈላጊ መመሪያዎች በአእምሯችን በመያዝ ምሳሌዎችን ለማጥናት ተዘጋጅተናል። በእያንዳንዱ ዓረፍተ ነገር፥ አገባቡ ይጠናል። ከዚያም በአገባቡ በመመራት ጥያቄውን ወይም ችግሩን ለማግኘት እንጥራለን። ይህም ምሳሌው የሚመልሰው ሲሆን የተገለጠ፥ በተዘዋዋሪ የተጠቆመ ወይም ተለይቶ የታወቀ ሊሆን ይችላል። በመጨረሻም ችግሩን ወይም ጥያቄውን ለመመለስ ይቻለን ዘንድ ምሳሌውን እንፈታዋለን። ከዚያም ትርጓሜው ለምሳሌው መንሥዔ የሆነውን ጥያቄ መመለስ አለመመለሱ ይፈተናል።